

AlexRenew

# በለዘላቂው ነገ ላይ ኢንቨስት ማድረግ

የRiverRenew መርሃ ግብርን ለመደገፍ AlexRenew የፍሳሽ ማስወገጃ ተመን ማስተካከያ እያደረገ ነው። ፕሮጀክቱ አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ በሚሊዮን ጋሎኖች የሚለካው የተቀናጀው ፍሳሽ በየአመቱ የአሌክሳንድርያን የውሃ መስመሮች እንዳይበክል ያደርገዋል። አማካይ የሆነው ወርሃዊ የነዋሪዎች የውሃ ክፍያ የወር ፍጆታቸው ወደ 4,000 ጋን ውሃ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ ሲሰላ በ$2.70 ገደማ ይጨምራል ተብሎ የተገመተ ሲሆን ይህም ከሐምሌ 1/2024 ጀምሮ የሚኖረውን የ5.1 በመቶ ጭማሪ የሚያመለክት ነው።

ስለክፍያ መጣኔ ማስተካከያው ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እና የአገልግሎት ክፍያዎን ለማስላት፣ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ **alexrenew.com/rates**።

Ver en Español

اقرأ باللغة العربية

View in English



# የAlexRenew የክረምት ወቅት የሩብ አመት አማካይ (Winter Quarter Average) ምንድን ነው?

የክረምት ወቅት የሩብ አመት አማካይ (Winter Quarter Average) ከታህሳስ እስከ የካቲት ባለው የደንበኛው (የክረምት ወቅት የሩብ አመት) የውሃ አጠቃቀም ታሪክ ላይ በመመስረት የሚሰራ የአገልግት ክፍያ ማስተካከያ ነው። ማስተካከያው ጥቅም ላይ የሚውለው ደንበኞች ለቤት ውስጥ የውሃ ፍጆታቸው ብቻ ክፍያ እንዲፈጽሙ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ነው - ይህም ማለት ቤት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እና ወደ AlexRenew የቆሻሻ ውሃ ማከሚያ ተቋም የሚፈሰው ውሃ ማለት ነው። ለአገልግቱ ብቁ የሆኑ ደንበኞች ከመጋቢት እስከ ህዳር ላለው ጊዜ ክፍያ እንዲከፍሉ የሚደረጉት ትክክለኛውን የውሃ ፍጆታቸውን መጠን ወይም የክረምት ወቅት የሩብ አመት አማካይን ከሁለቱ ዝቅተኛ የሆነውን በመጠቀም ነው።

ደንበኞችን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል ሲባል፣ የክረምት ወቅት የሩብ አመት አማካይ ስሌት በቅርቡ ተሻሽሏል። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ: **alexrenew.com/winteraverage**።

በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ይከተሉን።

AlexRenew